# በኢትዮጵያ የዓለምአቀፍ ውሎች

## መጽደቅና ደረጃቸው

በሺፈራው ወልደሚካኤል*

የድምዳሜያችን ጭብጥ የሆነው የዓለምአቀፍ ውሎች [1] መጽደቅና ደረጃቸው በሕገ መንግሥት የሕግ ቃሎች ውስጥ ያለ ልዩነት ይገለጻል ። ይህ አባባል ለሶሻሊስት ፣ ለምዕራባውያንና ለሶስተኛ ዓለም አገሮች ሁሉ ያገለግላል ።

ከላይ በተገለጸው አባባልና በታገደው የተሻሻለው የ1948 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት በመነሳት በኢትዮጵያ የዓለምአቀፍ ውሎችን መጽደቅና ደረጃቸውን እንመረምራለን ።

### የዓለምአቀፍ ውሎች መጽደቅ

የኃይለሥላሴን መንግሥት ያስወገደው ታሪካዊው አዋጅ ቁጥር 1 / 1967 ዓ.ም. ከመታወጁ በፊት የዓለምአቀፍ ውሎችን መጽደቅ ጥያቄ የሚመለከተው የተሻሻለው 1948 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30 ነበር ።

ይህ አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል ።

> « ንጉሠ ነገሥቱ ከውጭ አገር ጋራ የሚደረገውን ግንኙነት የበላይ ሆኖ ይመራል ። ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሮችን ሚኒስትሮችንና መልዕክተኞችን እየሾመ ይልካል ። በዚህም ዓይነት ከውጭ አገር እየተሾሙ የሚመጡትን ይቀበላል ። ከውጭ መንግሥት ጋር ያለውን ክርክር ሕጋዊ በሆነና በሰላማዊ መንገድ ለመወሰን ፣ እንዲሁም ጸጥታና የጋራ መከላከያ በሚጠበቅበት ረገድ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ ተባብሮ መሥራት የእርሱ መብት ነው ።
>
> በኢትዮጵያ ስም ውሎችንና ሌሎችንም የኢንተርናስዮናል ስምምነቶች ለማጽደቅና በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ላይ ሊፈጸሙ ግዴታ ከመሆናቸው አስቀድሞ የትኞቹ ውሎችና የኢንተናስዮናል ስምምነቶች መጽደቅ እንደሚገባቸው የመወሰኑ መብት የርሱ ብቻ ነው ይሁን እንጂ ፤ የሰላምን ውሎች ሁሉ ፤ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ግዛት አገር ወይም ከግዛቱ ማናቸውንም ክፍል ወይም ገዥነትን ወይም የዳኝነትን ሥልጣን የሚያሻሽሉ ወይም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ዜጎች ላይ ጉዳትን የሚያመጡ ወይም ጸንቶ የቆመውን ሕግ የሚያሻሽሉ ወይም የመንግሥት ገንዘብ ወጭ እንዲሆንባቸው የሚጠይቁ ወይም ብድሮች ወይም ሞኖፖል ያለባቸው ውሎችና የኢንተርናሲዮናል ስምምነቶች በንጉሠ ነገሥቱ ከመጽደቃቸው በፊት ለፓርላሜንት መቅረብ አለባቸው ። ሁለቱ ምክር ቤቶች በዚህ ሕገ መን

---

*በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ጽሕፈት ቤት የሕግ መምሪያ ኃላፊ

[1] « ዓለምአቀፍ ውል » የሚለውን ቃል በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የምንጠቀምበት ኢትዮጵያና አንድ ወይም ብዙ መንግሥታት ፤ ወይም በዓለምአቀፍ ሕግ የሚገዙ የሕግ ሰውነት ባላቸው ዓለም አቀፍ አካላት መካከል የሚደረግ ማናቸውም ስምምነት እንደሚሸፈን አድርገን ነው ።

> ግሥት በአንቀጽ 88 እስከ 90 በተጻፈው መሠረት የተቀበሏቸው እን ደሆነ ፤ እንዲጸድቁ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርባሉ ።"

ይህ አንቀጽ ንጉሠ ነገሥቱን

ሀ. ዓለምአቀፍ ውሎችን ወይም ሌሎች ዓለምአቀፍ ስምምነቶችን በሀ ገሪቱ ስም እንዲያጸድቅ ና

ለ. በአገሪቱ ውስጥ ተፈጻሚ እንዲሆኑ መጽደቅ የሚገባቸውን የዓለም አቀፍ ውሎች ዓይነት ለመወሰን ሥልጣን ይሰጠዋል ።

መስከረም 2 ቀን 1967 አንድ አዋጅ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ታወጀ ። ይህም አዋጅ ቁጥር 1 1967 ዓ. ም. ነበር ። ይህ አዋጅ የዘውድ አገዛዝን ያጠፋና ፤ የዘውድ አገዛዝ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሰፍኖባት በነበረች ምድር የኅብረተሰባዊነትን የመሠረት ድንጋይ የጣለ አዋጅ ነበር ። የታተመውም በነ ጋሪት ጋዜጣ 34ኛ ዓመት እትም ነበር ።

ይህ አዋጅም ያለጥርጥር ታሪካዊ አዋጅ ነው ። ነገር ግን እኛ ለአሁኑ ጽሑፍ በታሪካዊነቱ ሳይሆን ብዙውን የምናተኩረው በዓለምአቀፍ ውሎች መጽደቅ ላይ ያለውን ኃይል ነው በዚህም ላይ ስለ ዓለም አቀፍ ውሎች መጽደቅ በቀጥታ የሚጠቅስ በአጠቃላይ በአዋጁ ላይ የለም ። ነገር ግን ሁለት ቁጥሮች ማለትም የዚህ አዋጅ ቁጥር 5 / ሀ / እና ቁጥር 10 በዓለምአቀፍ ውሎች መጽ ደቅና ደረጃ ላይ ቀጥተኛ ኃይል አላቸው ።

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 5 ( ሀ ) እንደሚከተለው ያትታል ።

« የ1948 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት እንዳይሰራ ታግዷል ። »

ይህ ቁጥር ቀላልና የማያሻማ ነው ። ሕገ መንግሥቱ ታግዷል ። የዚህ ንዑስ ቁጥር በዓለምአቀፍ ውሎች መጽደቅ ላይ ያለው ውጤትም የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 30[2] ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ላለው ጊዜ በሥራ ላይ እንዳይውል ማድ ረግ ነው ።

በዚህም የዓለምአቀፍ ውሎችን መጽደቅ በሚመለከት አንዳንዶቹ በሕገ መንግሥቱ መታገድ ምክንያት ለተፈጠረው ባዶ ቦታ መሙያ የዚሁ አዋጅ ቁጥር 6 እንደሚጠቅም ያስባሉ ። ቁጥር 6 የሚከተሉት የሕግ ቃሎች ይገኙበ ታል ።

> « ሕዝቡ ሕጋዊ እንደራሴዎቹን መርጦ ሕገ መንግሥቱ
> እስኪታወጅና መንግሥት እስኪቋቋም ድረስ የጦር
> ኃይሎች ፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር ደርግ
> የመንግሥቱን ሥልጣን ይዞ አገሪቱን ይመራል ። »[3]

በደራሲው አስተያዬት ግን ይህ ቁጥር በዓለምአቀፍ ውሎች መጽደቅ ላይ ምንም ዓይነት ቀጥተኛ አግባብነት የለውም ። የሚያስተላልፈው መልዕክትም የጦር ኃይሎች ፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር ደርግ የንጉሠ ነገሥቱን ሥል

---

[2] አንቀጽ 30 በገጽ 1 እና 2 ላይ ተገልጿል ።

[3] የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1967 ዓ.ም. ፣ 34ኛ ዓመት ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1

ጣን እንደተከሉት ነው ። ይህም የዓለምአቀፍ ውሎች የሚጸድቁበትን ሥነ ሥር ዓትና የዓለምአቀፍ ውሎችን ለማጽደቅ ሥልጣን የተሰጠውን የአካሉን የተለየ ክፍል የሚያመለክት አይደለም ።

ለያዝነው የመወያያ አርዕስት መጠነኛ አግባብ ያለው ሌላው ቁጥር የዚህ አዋጅ ቁጥር 10 ነው ። ቁጥር .10 « እስካሁን በሥራ ላይ ያሉ ሕጐች ሁሉ ለዚህ አዋጅና ወደፊትም ለሚወጡት ሕጐች ፤ ትዕዛዞችና ደንቦች ተቃራኒ ካልሆኑ በስተቀር እንደጸኑ ይቆያሉ » ይላል ።

ከዚህ አዋጅ በፊት ካሉት ሕጐች ውስጥ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚጣጣሙትንና የማይጣጣሙትን ሕጐች ለይቶ የማውጣቱ ከባድ ኃላፊነት የሚመለከታቸው ፍርድ ቤቶችና በሌሎች በሕግ ሙያ ላይ በተሰማሩት ላይ ይሆናል ።

ለእኛ ተግባር ግን ከአንቀጽ 30 ሌላ ስለ ዓለምአቀፍ ውሎች መጽደቅ ጉዳይ አግባብ ያለው ሕግ ቢኖር ኖሮ አሁን በሥራ ላይ ካለው ሕግ ጋራ በመጣጣም ወይም ባለመጣጣሙ ምክንያት ከሥራ ላይ ሊውል መቻል ወይም አለመቻሉን በመረመርን ነበር ። ነገር ግን በአጋጣሚ በዚህ ነገር ላይ አግባብ ያለው የተሻሻለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30 ብቻ ነበር ። እርሱም ቢሆን በግልጽ ታግዷል ። በምንም ዓይነት የቃላት አተረጓጐም ወይም የሕግ አርቃቂውን ወይም የአዋጅ ቁጥር 1/1967ን ሕግ አውጭ ሀሳብ ለማወቅ በሚደረግ ጥረት የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 30 የማገድ ሀሳብ አልነበረም ለማለት አንችልም ። ይህ አንቀጽና ሌሎችም የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ሁሉ ታግደዋል ።

በዲሴምበር 12/1917 በሶቭየቶች የታተመውን ድንጋጌ ቁጥር 1 ስለፍርድ ቤቶች የሚለውንና ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር ጋር ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ የሕግ ቃል ስለአለው መመልከት ይጠቅመን ይሆናል ። ሳሙኤል ክቸሮስ እንዲህ ይላል ፥

> « የቀበሌ ፍርድ ቤቶች ውሳኔያቸውንም ሆነ ፍርዳቸውን ማስታወቅ የነበረባቸው በራሽያ ሪፐብሊክ ስምና በውሳኔያቸውም ሆነ ፍርዳቸውን <u>ሲሰጡ መመራት ያለባቸው በተገረሠሠው መንግሥት ሕግ የሚሆነው እነኝህ ሕጐች በአብዮቱ እስካልተደመሰሱና ከአብዮታዊ ንቃተ ሕሊናና አብዮታዊ የሕግ ሀሳብ እንዲሁም ከሶሻል ዲሞክራቲክና ከሶሻል አብዮታዊ ፓርቲዎች ፕሮግራም ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ብቻ ነው ።</u>[4] ( ስርዝ የተጨመረ )

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ማቋቋሚያ አዋጅ የታወጀውና በሥራ ላይ የዋለው ከመስከረም 2/1967 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን ፥ ከሶስት ቀን በኋላም « የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀመንበሩን ሥልጣን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 2/1967 ዓ.ም. » አዋጅ ታወጀ ።[5] ይህም አዋጅ አሥራ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት እኛ ግን የምናተኩረው በአራተኛው ቁጥር ላይ ይሆናል ። ይህም ቁጥር እንደሚከተለው ይነበባል ።

---

[4] ሳ. ክቸሮቭ <u>ዘ ኦርጋንስ ኦፍ ሶቭዬትስ አድሚኒስትሬሽን ኦፍ ጀስቲስ ዜር ሂስትሪ ኤንድ ኮአፐሬሽን</u> ( ሌይደን ኢ.ጃይ ድሪል ) ፥ ( 1970 ገጽ 24 )

[5] 34ኛ ዓመት ነጋሪት ጋዜጣ ፥ ቁጥር 2

« በኢትዮጵያ ስም ውሎችንና ሌሎችንም የዓለምአቀፍ ስምምነቶች ማጽደቅና በመንግሥቱ ላይ ሊፈጸሙ ግዴታ ከመሆናቸው አስቀድሞ የትኞቹ ውሎች ዓለምአቀፍ ስምምነቶች መጽደቅ እንደሚገባቸው የመወሰን ሥልጣን የደርጉ ነው [6] ።"

ስለሆነም የሰላም ውሎች ፤ በመንግሥቱ የሚተ ዳደረውን አገር ወይም በአገሩ በማንኛውም ክፍል ላይ ያለውን አስተዳደር ወይም ሙሉ ሥልጣን የሚያሻሽሉ ወይም በመንግሥቱ ዜጐች ላይ ጉዳትን የሚያመጡ ወይም ጸንቶ ያለን ሕግ የሚያሻሽሉ ወይም የመንግሥት ገንዘብ ወጭ እንዲሆንባቸው የሚጠይቁ ወይም ብድሮች ወይም የሞ ኖፖል ጠባይ ያለባቸው ውሎችን ዓለምአቀፍ ስምምነቶች ሁሉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተመከረባቸው በኋላ ለደ ርጉ ቀርበው ይጸድቃሉ ። »

በዚህ ቁጥር ውስጥ የሠፈሩ ቃላት ከታገደው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30 ቃላት ጋር ጥቂት ተመሳሳይነት ያላቸው ይመስላል ። የሆነው ይሁንና ከዚህ ቁጥር ከሚከተለው መደምደሚያ መድረስ ይቻላል ።

ሀ. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የዓለምአቀፍ ውሎችን በኢት ዮጵያ ስም የማጽደቅ ሥልጣን አለው ።

ለ. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የትኞቹ ዓለምአቀፍ ውሎች በአገሪቱ ውስጥ ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ እንዳለባቸው የመወሰን ሥልጣን አለው ።

ሐ. የሚከተሉት ዓይነት የዓለምአቀፍ ውሎች በጊዜያዊ ወታደራዊ አስ ተዳደር ደርግ ከመጽደቃቸው በፊት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊመ ከርባቸው ይገባል ።

1. የሰላም ዓለምአቀፍ ውሎች ።
2. በመንግሥቱ የሚተዳደረውን አገር ወይም በአገሩ በማንኛውም ክፍል ላይ ያለውን አስተዳደር ወይም ሙሉ ሥልጣን የሚያሻ ሽሉ ዓለምአቀፍ ውሎች ።
3. በመንግሥቱ ዜጐች ላይ ግዴታን የሚያመጡ ዓለምአቀፍ ውሎች
4. ጸንቶ ያለን ሕግ የሚያሻሽሉ ዓለምአቀፍ ውሎች ።
5. የመንግሥት ገንዘብ ወጭ እንዲሆንባቸው የሚጠይቁ ዓለምአቀፍ ውሎችና
6. ብድሮች ወይም የሞኖፖል ጠባይ ያላቸው ዓለምአቀፍ ውሎች ።

በክፍል ሶስት ውስጥ የሚጠቃለሉ ዓለምአቀፍ ውሎች ሆነው በሚኒስት ሮች ምክር ቤት ግን ሳይመክርባቸው በቀሩ ወይንም ደግሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመክሮባቸው ነገር ግን ምክር ቤቱ ያልተስማማባቸው ዓለምአቀፍ ውሎች ምን እንደሚሆኑ በትክክል አይታወቅም ። ቁጥሩ የሚለው በክፍል ሶስት የተ ጠቀሱት ዓይነት ዓለምአቀፍ ውሎች ሁሉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተመከ

6. « ደርግ » የሚለው ቃል የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን ያመለክታል ።

ረባቸው በኋላ ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ቀርበው ይጸድቃሉ ብቻ ነው ። ( ስርዝ የተጨመረ )

ይህ አዋጅ ዓለምአቀፍ ውሎች የሚጸድቁበትን ሁኔታ በሚመለከት በነበረው ግርዶሽ ላይ ብርሃን የሚፈነጥቀው ሙሉ በሙሉ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር110/1969 ዓ.ም. ተተክቷል ።[7] ይህ አዲስ አዋጅ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀመንበሩን ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1967 ቁጥር 4[8] ፋንታ ምንን ተክቷል ? ለዚህ ጥያቄ መልስ አዋጅ ቁጥር 110/1969ን እንመረምራለን ።

የዚህ አዋጅ ቁጥር 5 የጠቅላላ ጉባኤውን ሥልጣንና ኃላፊነት ይገልጻል ።[9] በዚህ ቁጥር ንዑስ ቁጥር 4 መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው « በኢትዮጵያ ስም መሠረታዊ የሆኑ የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካ ፤ የመከላከያና የጋራ መከላከያ ውሎችንና ኢንተርናሽናል ስምምነቶችን የማጽደቅ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው ። » ( ስርዝ የተጨመረ )

በዚህ ንዑስ ቁጥር ለተወሰኑ ውሎች የማጽደቅ ሥልጣን ያለው አካል በግልጽ ተጠቁሟል ። መጽደቅ የሚያስፈልጋቸውንና የማያስፈልጋቸውን ውሎች የመለየት ጥረት መደረጉም በግልጽ ይታያል ። ነገር ግን እስኪ ይህንን ንዑስ ቁጥር በአንዳንድ መለኪያዎች እንለካና ውጤት ማስገኘቱን እንመልከት ። « መሠረታዊ » የሆኑ የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካና የመከላከያ ውሎች ምንድን ናቸው? ወይም በተቃራኒው መሠረታዊ ያልሆኑ የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካና የመከላከያ ውሎች ምንድን ናቸው ? እንደሌሎች ሕጎቻችን ይህ አዋጅ የፍቺ ( የትርጓሜ ) ቁጥሮች ስለሌለው ወደዚያ በመሄድ እነኝህን ግልጽ ለማድረግ አይቻልም ። አንድ ዓለምአቀፍ ውል መሠረታዊ መሆን አለመሆኑ እንዴት ይወሰናል ? « ባሕልን » ስለሚመለከቱ ውሎችስ ? አንድ « መሠረታዊ » ውል በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ጠቅላላ ጉባኤ ፥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም በሌላ አካል ከመጽደቁ በፊት ሊመከርበት ይገባልን ? ( ለምሳሌ ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፤ ለኢኮኖሚ ውሎች ) እነኝህን ጥያቄዎች ያነሳናቸው ብዙ ሰዎች የሕግ ሰዎች ጥያቄ ማንሳት ይወዳሉ ብለው እንደሚከሱን ዓይነት ጥያቄዎችን ለማንሳት ስንል ሳይሆን ጥያቄዎቹ ጠቃሚዎችና መልስ የሚያስፈልጋቸው በመሆናቸው ነው ።

ከላይ የተጠቀሰው ቁጥር መጽደቅ የሚያስፈልጋቸውን ውሎች በመለየት በኩል ብዙም ሊረዳ አይችልም ። የሚያስረዳን ነገር ቢኖር « መሠረታዊ የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካ ፥ የመከላከያና የጋራ መከላከያ እንዲሁም ዓለምአቀፍ ስምም

---

7 የዚህ አዋጅ ቁጥር 21 እንዲህ ይላል ።
« የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1969 ዓ.ም. ፥ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀመንበሩን ሥልጣን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1967 ዓ.ም. እንደተሻሻለ ፥ እንዲሁም ስለ ሚኒስትሮች ሥልጣንና ሥራ አወሳሰን በቍጥር 1/1935 ዓ.ም. በወጣው ትእዛዝ እንደተሻሻለው ከ 1 እስከ 14 ቍምር ያሉት አንቀጾች በዚህ አዋጅ ተሽረው ተተክተዋል ።
( ስርዝ የተጨመረ )

8 የአዋጅ ቁጥር 2/1967 ዓ.ም. ቁጥር 4 ከዚህ በላይ በገጽ 5 ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተጠቅሷል ።

9 የጊዜያዊ ወታደራዊ አስበዳደር ደርግ ፥ ጠቅላላ ጉባኤ ፥ የማዕከላዊ ኮሚቴና ቋሚ ኮሚቴ የተባሉ አካላት አሉት ። የበለጠ ለመረዳት የዚህኑ አዋጅ ቁጥር 2 ይመለከቷል ።

ነቶች » ማን እንደሚያጸድቃቸው ብቻ ነው ። ቀላሉና እንደደራሲውም አመለካከት የተሻለው አማራጭ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ጠቅላላ ጉባኤ መጽደቅ የሚገባቸውን የአለምአቀፍ የውል ዓይነቶች በተሻረው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀመንበሩን ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1967 ቁጥር 4 መሠረት መዘርዘሩ ነው ። ይህንን ሐረግ ልንተረጉም የምንችልበት አንዱ አማራጭ መሠረታዊ ያልሆኑ ዓለምአቀፍ ውሎች በመንግሥት ላይ አስገዳጅነት ይኖራቸው ዘንድ መጽደቅ እንደማያስፈልጋቸው ነው ።

ከላይ ባነሳናቸው ጥያቄዎች መሠረት

ሀ/ ከብዙ አገሮች ጋራ የገባናቸው በመንግሥታት መካከል የሚኖሩ የጋራ የኢኮኖሚ ኮሚሽኖች ማቋቋሚያ ዓለምአቀፍ ውሎች

ለ/ ኢትዮጵያ ከለሎች አገሮች ጋር የገባቻቸው ጓዳዊና የትብብር የተለያዩ ውሎችና

ሐ/ የውጭ ንግድ ሚኒስቴር ከሌላ ሀገር አቻዎቹ ጋራ የገባቸው ብዙ የንግድ ውሎች መጽደቅ የሚገባቸው መሆኑን ማወቅ ያስቸግራል ።

ከላይ የተጠቀሱት ዓለምአቀፍ ውሎች መጽደቅ የሚያስፈልጋቸው መሆን አለመሆኑ « መሠረታዊ » በመሆንና በአለመሆናቸው የሚወሰን ነው ። ማንም ቢሆን የተጠቀሱትን ዓለምአቀፍ ውሎች በጥልቀት ከመመርመሩ አስቀድሞ በጭብጡ ላይ አቋም ለመውሰድ አይቻለውም ፤ ያም ሆኖ ግን ሁለት ሰዎች አንድ ዓለምአቀፍ ውል « መሠረታዊ » መሆን አለመሆኑን በሚመለከት ሳይስማሙ ቢቀሩ ዳኛ ማስፈለጉ አይቀርም ።

ይህ ጥያቄ በተግባር እንዴት ይሠራበታል ? አቶ ፍስሐ ይመር እንዲህ ይላሉ ።

« አሁን በምንሠራው መሠረት ዓለምአቀፍ ውል በማጽደቅ ላይ ቃል ካልጨመረ ወይም ምንም ካላለ ውሉ ወይም ስምምነቱ እንዲጸድቅ የሚደረገው የውሉን ወይም የስምምነቱን ባሕርይ ለመወሰን ይዘቱን በመመርመር ነው ። ይህ ግን የሚሆነው አንዳንድ ጊዜ ነው ። በአብዛኛው ውሎችና ስምምነቶች ላይ ግን ግልጽ የሆነ መጽደቅ እንዳለበት የሚያሳይ ቃል አለ ። ሁላችንም እንደምናውቀው መጽደቅን በሚመለከት የሚወስነው ሕግ አውጭው ወይም ሌላ የሕግ ማውጣት ሥልጣን ያለው ነው ። በእኛ አስተያየት እንኳ ምንም ውሉ መሠረታዊ አይደለም ብንል በጠቅላላ ጉባኤው መጽደቅ አለበት የሚል ካለ መደረግ ይኖርበታል ።

ይህንን አለማድረግ ማለት ደግሞ ውሉ በኢትዮጵያና በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ ተፈጻሚ አይሆንም ማለት ነው ። ምክንያቱም ሌላው ወገን በሁለቱም ወገኖች መጽደቅ አለበት ብሎ በግልጽ ስለሚጠይቅ ነው ። ለዚህ ችግር መፍትሄው ውሉ መሠረታዊ ካልሆነ በድርድሩ ወቅት የማጽደቂያ ሐረግ አለመጨመር ነው ። ውሉ እንዲሁ በፊርማ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል ። እኛም የሚኒ

ስቴር መሥሪያ ቤቶችን በግልጽ መሠረታዊ ባልሆኑ ውሎች ወይም ስምምነቶች ላይ የማጽደቂያ ሐረግ እንዳይጨምሩ እንመ ክራለን ። »[10]

## የዓለምአቀፍ ውሎች ደረጃ

ቀጥሎ የምንወያየው የዓለምአቀፍ ውሎችን ደረጃ በአሁኒቱ ኢትዮጵያ ይሆ ናል ። በመጀመሪያ ደረጃ መጥቀስ የምንፈልገው አሁን «ደረጃ» የሚለውን ቃል ስንጠቀምበት ሁለት ፍቺ እንዳለው ነው ። በአንድ መልኩ ዓለምአቀፍ ውሎች አሁንም ድረስ ሕጋዊ መሆን ያለመሆናቸውን ያመለክታል ። በሌላው መልኩ ደግሞ ለማሳየት የተሞከረው እስካሁን ሕጋዊ የሆኑት ዓለምአቀፍ ውሎች ከእኛ የአገር ውስጥ ሕጎች ጋር የበላይ ወይም አቻ እንደሆኑ ለማሳየት ነው ።

በመንግሥትነት አሁን የምንገኝበት ሁኔታ ቀደም ሲል ከነበረው ጋር በከ ፊል የተቀራኘ ስለሆነ የኃይለሥላሴ አገዛዝ ከወደቀበትና የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ከመስከረም 2/1967 ዓ.ም. በፊት በዚህ ረገድ የነበረውን የሕግ ሥርዓት ለማጤን አሥራሁለት ዓመታት ወደኋላ እንጓዛለን ።

ከተጠቀሰው ቀን በፊት የዓለምአቀፍ ውሎች ደረጃ የሚገዛው በተሻሻለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 122 መሠረት ነበር ፤ የተባለው አንቀጽ እንዲህ ይላል ።

> « ይህ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያ ተካፋይ
> ከምትሆንባቸው ከኢንተርናሲዮናል ውሎች ከዓለም አቀፍ
> ስምምነቶችና ግዴታዎች ጋራ በአንድነት ሆኖ የን
> ጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የበላይ ሕግ ይሆናል ።
> ወደፊትም የሚሰሩ ሕጎች ፣ ድንጋጌዎች ፣ ፍርዶችና
> ውሳኔዎች ሁሉ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋራ የማይስማሙ
> ሲሆኑ ዋጋ የሌላቸውና የማያገለግሉ ይሆናሉ ።

ለእኛ ተግባር ይህ አንቀጽ ግልጽ በመሆኑ የሚብራራ ነገር የለውም ። በኢ ትዮጵያ የተገቡ ዓለምአቀፍ ውሎች ከሕገ መንግሥቱ ጋራ እኩል ደረጃ ሲኖራ ቸው በሕግነታቸውም የአገሪቱ የበላይ ሕጎች ናቸው ። ስለሆነም ማናቸውም የአሁን ወይም የወደፊት ሕጎች ፣ ድንጋጌዎች ፣ ፍርዶች ኢትዮጵያ ከምትገባ ቸው ዓለምአቀፍ ውሎች ጋር የማይስማሙ ከሆኑ ዋጋ የሌላቸውና የማያገለግሉ ይሆናሉ ።

የተሻሻለው ሕገ መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 1/1967 ዓ.ም. ቁጥር 5 /ሀ/ እንደታገደ ቀደም ሲል አይተናል ። በአንቀጽ 122 መሠረት ዓለምአቀፍ ውሎች ሁሉ « የንጉሠ ነገሥቱ የበላይ ሕጎች » ስለነበሩና በአዋጅ ቁጥር 1/1967 ዓ.ም. ቁጥር 10 መሠረት ደግሞ ከአዋጁና ወደፊት ከሚወጡ ሕጎች ጋር የሚቃረኑ ሕጎች ብቻ ዋጋ እንደሌላቸው ስለሚቆጠሩ ቢያንስ እነዚህ በዚህ ክፍል የማይ መደቡ ዓለምአቀፍ ውሎች ማለትም ከአዋጁ ጋር አይስማሙም ያልተባሉ ዓለም አቀፍ ውሎች አሁንም በሥራ ላይ ናቸው ማለት ይቻላል ?

ይህ እንግዲህ እጅግ አወያይ ወደሆነው ወደ ዓለምአቀፍ ውሎች ውርስ ያመጣናል ።

[10] ከአቶ ፍስሐ ይመር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕግ መምሪያ ኃላፊ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ፣ ጥር 1975

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሥራውንና ፖሊሲውን ሁሉ በከረረና ባላሰለሰ መልክ የወቀሰው የቀድሞ መንግሥት የገባቻውን ውሎች ሁሉ ይወርሳል ወይ ?

ይህ እንግዲህ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ አመለካከት የተሰነዘረበት የዓለምአቀፍ ሕግ ክፍል ነው ። ቢሆንም ግን መሠረታዊ የሁኔታዎች ለውጥ ውሎችን ለመሻርና ለማገድ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ አጠቃላይ ስምምነት ያለ ይመስላል ። ይህ « የሪባስ ሲክ ስታንቲባስ » መመሪያ ሲሆን የዓለምአቀፍ ውሉን ዓይነት ተከትሎ የመንግሥት ለውጥ መሠረታዊ ለውጥ ሊሆን ይችላል ። ከሞላ ጐደል አጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘውና የዓለምአቀፍ ውሎችን ሕግ በሚመለከተው የቪየና ስምምነት ውስጥ ተመሳሳይ አመለካከት ተንጸባርቆ ይገኛል[11]።ይህን ስምምነት ኢትዮጵያ የፈረመችው እ.ኤ.አ. በኤፕሪል30/1970 ዓ.ም. ነው ። በእኛ አገር የተደረገው ለውጥ የመንግሥት ለውጥ ብቻ አይደለም ። ለውጡ ካለፈው መንግሥት በጣም የተለየ የኢኮኖሚ ፣ ሶሻልና የፖለቲካ አመለካከት የታየበት ለውጥ ነው ። አዲስ ኅብረተሰብ ፣ ከአዲስ አመለካከትና ግብ ጋር እየገነባን ነው ። ከዚህ አንጻር ተዋዋዮቹን ወገኖች ወታደራዊና የደህንነት መረጃዎች ለመለዋወጥ የሚያስገድዱ ወታደራዊ ወይም ፖለቲካዊ ውሎች በሥራ ላይ እንዳሉ ናቸው ማለቱ የማያስኬድ ባይሆንም ይህ አመለካከት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተዋዋዮች ጉዳት በማያስከትልባቸው ርምጃ እንዲስማሙ ይህንን ከመሰለው ሁኔታ ለመጠበቅም ነው። ቁጥር56 በቪየና ኮንቬንሽን የገባው ይህን ዓይነት ሁኔታ ለመጠበቅ ይሆናል።[12] ይህን ጉዳይ ከመደምደማችን በፊት ሳይጠ

---

[11] ቁጥር 62 መሠረታዊ የሁኔታዎች ለውጥ

1. ዓለምአቀፍ ውሉ በተደረገበት ጊዜ የነበሩትን ሁኔታዎች በሚመለከት በተዋዋዮቹ ወገኖች ያልታሰበ መሠረታዊ ለውጥ የተፈጠረ እንደሆነ ውሉን ለማስቀረትም ሆነ ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ፤
   - ሀ/ የእነኛ ሁኔታዎች መኖር ለተዋዋዮቹ ወገኖች ግዴታ መግባት አስፈላጊ መሠረቶች የነበሩ እንደሆነና
   - ለ/ የለውጦች መኖር በውሉ ላይ የተጠቀሰውን የግዴታ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ የሚለውጠው ሆኖ ሲገኝ ነው ።
2. መሠረታዊ የሁኔታዎች ለውጥ ውልን ለማስቀረትም ሆነ ለመሰረዝ እንደ ምክንያት ሆኖ የማይቀርበው ፤
   - ሀ/ ዓለምአቀፍ ውሉ ድንበርን የሚያቋቁም ከሆነ ወይም
   - ለ/ መሠረታዊ ለውጡ የተፈጠረው ውሉ ይፍረስልኝ በሚለው ወገን ዓለም አቀፍ ውሉ የሚጥልበትን ግዴታ ወይንም ሌላ ከውሉ ውስጥ ያለ ለሌላ ወገን ያለበትን ዓለምአቀፍ ግዴታ ባለመፈጸሙ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ነው ።
3. ከላይ በተጠቀሱት መሠረታዊ የሁኔታዎች ለውጥ ምክንያት አንድ ተዋዋይ ወገን ዓለምአቀፍ ውሉን ለማስቀረት ወይም ለመሠረዝ የሚችል ከሆነ ይህንን ለውጥም ዓለምአቀፍ ውሉን በሥራ ላይ መዋል ለጊዜው እንዲታገድ በማድረግ ምክንያት ቢያደርገው ይችላል ።

[12] ቁጥር 56 ማስቀረትን ፣ ውድቅ ማድረግን ወይንም መሠረዝን የሚመለከት ቃል ያልተጨመረበትን ዓለምአቀፍ ውል ስለማሳጣትና ወይም ስለመሠረዝ

1. ሀ. አንድ ዓለምአቀፍ ውል መቅረቱን በሚመለከት ወይንም ውድቅ መደረጉን ወይንም መሠረዙን የሚመለከት ቃል በውሉ ውስጥ ከሌለበት ለማሳጣትም ሆነ ለመሠረዝ የሚችለው ።
   ለ. ከራሱ ከዓለምአቀፍ ውሉ ውስጥ የማሳጣትም ሆነ የመሠረዝ መብትን ማሳየት ከተቻለ ነው ።
2. አንድ ተዋዋይ ወገን በአንቀጽ 1 መሠረት አንድን ዓለምአቀፍ ውል ለማሳጣት ወይም ለመሠረዝ ሀሳብ ካለው ይህንኑ ሀሳቡን ከ12 ወራት ባላነሰ ጊዜ ማሳወቅ አለበት ።

ቀስ ሊታለፍ የማይገባ ነጥብ አለ ። ስምምነት ውስጥ እንዲገባ የተደረገው ዓለምአቀፍ ውሉየመንቀፍ ወይም የመሠረዝ ቃልን ከጨመረ ከግዴታ ነጻ ለመሆን ያ ቃል መከበር አለበት ። በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰነዘሩት አስተያየቶች ይህን ግዴታ ገሸሽ ለማድረግ እንደሚያስችሉ ተደርገው መቆጠር የለባቸውም ።

በሌላ መንገድ ደግሞ ባለፈው መንግሥት የተገቡት ሁሉም ዓለምአቀፍ ውሎች በአሁኑ መንግሥት ላይ አስገዳጅነት የላቸው ም ለማለት አይቻልም ። የተባበሩት መንግሥታት ፥ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና እንዲሁም የሌሎች ዓለምአቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች አባልነታችን ያለፈው መንግሥት በገባቸው ዓለምአቀፍ ውሎች ላይ የተመሠረተ ነው ።

ከዚህ በላይ ያሉት ሁለት ፓራግራፎች የገቡት የዓለም አቀፍውሎች ደረጃ ማለትም አሁንም ድረስ የጸኑ የመሆናቸው ወይም ያለመሆናቸው ጉዳይ አስቸጋሪና አጠቃላይ መልስ ለመስጠት እንደማያቻል ለአንባቢው ለመጠቆም ነው ። እያንዳንዱ ዓለምአቀፍ ውል ለየብቻው መመርመርና አቋምም መወሰድ አለበት ። ሆኖም ግን በደራሲው አስተያየት ከላይ ከተጠቀሱት ( በመሠረታዊ የሁኔታዎች ለውጥ ምክንያት ተሰርዘዋል ሊባሉ ከሚችሉት ) ውሎች በስተቀር ባለፈው አገዛዝ በጊዜው በነበሩት ሕጎች መሠረት የተገቡ ሁሉም ውሎች አሁንም ዋጋ አላቸው ማለቱ ይበልጥ ትክክልና ተጨባጭ ይሆናል ።

ባለፈው አገዛዝ የተገቡ ውሎች ዋጋ አላቸው ወይ ለሚለው ጭብጥ እልባት ለመስጠት ከሞከርን ዘንድ አሁን ደግሞ የደረጃቸውን ጉዳይ እንመለከታለን ። ይኸውም ውሎቹ ከአገር ውስጥ ሕጎች ጋር ሲነጻጸሩ የበላይነት ያላቸው መሆን አለመሆኑን ወይም በእኩልነት ደረጃ የሚገኙ መሆኑን እንመረምራለን ።

ባለፈው አገዛዝ የተገቡ ውሎች ሁሉ በሕገ መንግሥቱ የሕግ ቃላት መሠረት የበላይነት ሕግ ደረጃ እንዳላቸው ከፍ ሲል ተመልክተናል ። በተጨማሪም እነኚህ ውሎችን የበላይ ሕግ እንዲሆኑ ያበቁዋቸው የሕግ ቃላትም ሆኑ ሕገ መንግሥቱ ራሱ እንደታገዱ አይተናል ። ታዲያ ውሎች በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ደረጃቸው እንዴት ነው ?

ባለፈው መንግሥት በኢትዮጵያ ስም የተገቡ አንዳንድ ዓለምአቀፍ ውሎች በአዋጅ[13] ወይንም በድንጋጌ[14] መልክ በነጋሪት ጋዜጣ ይታተሙ ነበር ። አንዳንዶቹ ደግሞ በነጋሪት ጋዜጣ አይታተሙም ነበር ። ነገር ግን ውሎች በአገሪቱ ላይ አስገዳጅነት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ አስፈላጊ ሀጋዊ ሥርዓቶች ይሟላላቸው ነበር ።

የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ቻርተር ፥ የአፍሪቃ ፋይቶሳኒታሪ ኮንቬንሽን ፥ ከሌሎች ሀገሮችና ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ጋር ለተደረጉ የብድር ስምምነቶች የአገር ውስጥ ሕግ ደረጃ የሚሰጡ አያሌ የብድር ማጽደቂያ አዋጆች በመጀመሪያው ክፍል የሚጠቃለሉ ዓይነት ዓለምአቀፍ ውሎች ምሳሌዎች ናቸው ። እነኚህ ዓለምአቀፍ ውሎች የአገር ውስጥ ሕጎቻችን አካላት ናቸው ። የነዚህ

[13] « አዋጅ » በተሻሻለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34ና 88 መሠረት በፓርላማው ተቀባይነት ያገኘና በንጉሠ ነገሥቱ የጸደቀ ህግ ነበር ።

[14] « ድንጋጌ » እማካሪዎች ባልተሰበሰቡበት ጊዜ የሚያስቸኩል ጉዳይ የተገኘ እንደሆነ በንጉሠ ነገሥቱ የሚታወጅ መብትና ግዴታን የሚደነግግ ህግ ነበር ። የተሻሻለው ሕገ መንግሥት 92

ዓለምአቀፍ ውሎች ዘለቄታ የወደቀው መንግሥት ካወጃቸው ህጎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ነው ። ያለፈው መንግሥት ያወጃቸውን ህጎች በሚመለከት መመዘኛ መለካት ይኖርባቸዋል ። ይኸውም « ከአዋጅ ቁጥር 1/1967 ዓ.ም. ጋር ይቃረኑ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ነው ።»[15] ከዚህ አዋጅ ጋር የማይቃረኑ ከሆነ በአሁኑ ጊዜ ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑ አያጠያይቅም ።

ከባድ ችግር የሚያጋጥመን ግን አንድ ዓለምአቀፍ ውል በነጋሪት ጋዜጣ ከታወጀ ማለትም የአገሪቱ የውስጥ ህግ አካል ከሆነና ይህም ከአዋጅ ቁጥር 1 /1967 የህግ ቃላት ጋር የተቃረነ እንደሆነ ነው ። የአዋጅ ቁጥር 1/1967 ቁጥር 10 እነኝህን ዓለምአቀፍ ውሎች የአገሪቱ የአገር ውስጥ አካልነታቸውን በግልጽ ይነፍጋቸዋል ። እንደዚህ ዓይነት ችግር የገጠመው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤትም የአዋጅ ቁጥር 1/1967 ዓ.ም. ን ቁጥር 10 በመጥቀስ ዓለምአቀፍ ውሉን ተግባራዊ እንዳይሆን የሚያደርግ መሆኑም ሊጠበቅ የሚችል ነው ። ይህ ግን በዓለምአቀፍ ደረጃ ብዙም ክብደት የለውም ። ምክንያቱም የዓለምአቀፍ ውሎች ሕግ ስምምነት በቪየና ኮንቬንሽን ቁጥር 27[16] መሠረት የአገር ውስጥ ህግ በዓለም አቀፍ ውል ላይ የተመሠረተን ግዴታ ላለመወጣት መከላከያ ሆኖ መቅረብ ስለማይችል ነው ። ነገር ግን የአሁኑ መንግሥት በእንዲህ ዓይነት ዓለምአቀፍ ውሎች ላይ ከተመሠረተ ግዴታ ነጻ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ቀላል አይደለም ። የዚህ ጥያቄ መልስም በአብዛኛው የሚመሠረተው በዓለምአቀፍ ውሉ ይዘት ላይ ነው ። ለእኛ ተግባር ግን የዓለም አቀፍ ውሎች ውርስ ንድፈ ሀሳብ ይህንን ችግር ለመፍታት ወሳኝ ሚና ይጫወታል ብንል በቂ ነው ።

እስኪ አሁን ደግሞ ባለፈው መንግሥት የተገቡና በአገሪቱ ላይ ህጋዊነት እንዲኖራቸው ሁሉም አስፈላጊ የሆኑ ሥርአት የተሟሉላቸው መጽደቃቸውን ግን በነጋሪቱ ጋዜጣ ስላልታተሙ ዓለምአቀፍ ውሎች ባጭሩ እንመልከት ። በዚህ ክፍል በሚጠቃለሉት ዓለምአቀፍ ውሎችና የአገር ውስጥ ሕግ አካል በሆኑ ዓለምአቀፍ ውሎች ( ይኸውም በነጋሪት ጋዜጣ በሕግነት የታተሙ ዓለምአቀፍ ውሎች ) መካከል ያለው አንድ በጣም ትልቅ ልዩነት ይህ ነው ። የአዋጅ ቁጥር 1/1967 ዓ.ም. ቁጥር 10 በነዚህ ዓለምአቀፍ ውሎች ላይ እንደመቃወሚያ ነጥብ ሊነሳ አይችልም ። ምክንያቱም ቁጥር 10 የሚመለከተው ህጎችን ብቻ ስለሆነ ነው ። ዓለምአቀፍ ውሎችን የበላይነት ደረጃ ይሰጣቸው የነበረው የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ቁጥር 122ና ሕገ መንግሥቱም ራሱ በመታገዱና እንዲሁም እነኝህ ዓለምአቀፍ ውሎች ራሳቸው እንደ ሕግ ባለመታተማቸው በአዋጅ ቁጥር 1/1967 ዓ.ም. ቁጥር 10 መሠረት በሥራ ላይ ሊውሉ አይችሉም ማለት አይቻልም ።

በዚህ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ አስተያየት መስጠት ያስቸግራል ። እያንዳንዱ ዓለምአቀፍ ውል በየራሱ ጥንካሬ መዳኘት አለበት ። ቢሆንም በደራሲው አስተያየት ግን የተባሉት ዓለምአቀፍ ውሎች መነቀፍ ወይም መሠረዝ የሚችሉት በቪየና የዓለምአቀፍ ውሎች ሕግ ስምምነት ቁጥር 56 መሠረት የመንቀፍ ወይም የመሠረዝ መብት መኖሩን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ነው ።

---

[15] ይህ ቁጥር ከዚህ በላይ በገጽ 3 ተተንትኗል ።

[16] ቁጥር 27 የአገር ውስጥ ህግና ዓለምአቀፍ ውሎችን ስለማክበር « አንድ ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ላለመወጣቱ የራሱን የአገር ውስጥ ህግ እንደ ምክንያት ማቅረብ አይችልም ።

በአለፈው መንግሥት ስለተገቡት ዓለምአቀፍ ውሎች እላይ ያልነው ይበቃል ። ነገር ግን በአሁኑ መንግሥት የተገቡት ዓለምአቀፍ ውሎች ደረጃ ከሀገር ውስጥ ሕጐች ጋር ሲነጻጸር እንዴት ነው እኩል ናቸው ወይስ የበላይነት አላቸው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እንደ ርዕሰ ብሔርና እንደ ርዕሰ መንግሥት ፤ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት እድገት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ሌሎችም የመንግሥት ድርጅቶች ብዙ ዓለምአቀፍ ውሎችን ከአቻዎቻቸው ጋር ገብተዋል ( ፈርመዋል ) ።

ለአንዳንድ ዓለምአቀፍ ውሎች የማጽደቂያ አዋጆች በነጋሪት ጋዜጣ ታትሟል ። ለሌሎች ግን እንዲህ ዓይነት አዋጅ የለም ።

ዓለምአቀፍ ውሎችን የሚያጸድቁ ሕጐችን ማወጁ ሊያስከትል የሚችለው አንድ ውጤት ዓለምአቀፍ ውሎችን የአገር ውስጥ ሕግ አካል ማድረግ ነው ብለን ብንገምት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በወጣ ሕግ የጸደቁ ዓለምአቀፍ ውሎች ደረጃው ከአጸደቃቸው ሕግ ጋር እኩል ደረጃ ነው ብሎ መከራከር ይቻላል ። እኩል ደረጃ ካላቸው ሕጐች የበላይ መሆን አይችልም ። ሌላ የተቃረነ የሕግ ቃል በሌለበት ጊዜ ይህ አባባል ተገቢ ድምዳሜ ይመስላል ።

የሚቀጥለው ደግሞ በአሁኑ መንግሥት የተገቡ ዓለም አቀፍ ውሎች ሆነው የማጽደቂያ ሕግ በነጋሪት ጋዜጣ ያልታወጀባቸው የዓለም አቀፍ ውሎች ደረጃ ጉዳይ ይሆናል ። በደራሲው አስተያየት እነኝህ ዓለም አቀፍ ውሎች የማጽደቂያ አዋጅ ከታወጀላቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ከፍ ወይም ዝቅ ያለ ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል ማለቱ ተገቢ አባባል ነው ።

## መደምደሚያ

በአሁኑ ሰዓት አንባቢው የችግሩን ሁኔታ እንደተመለከተ ተስፋ ይደረጋል ። መጽደቅ የሚገባቸውን የዓለምአቀፍ ውል ዓይነቶች መለየቱ አንገብጋቢ ግዴታ ነው ። ብዙ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ከሌላ አገር አቻዎቻቸው ጋር የተለያዩ ስምምነቶችን ይፈርማሉ ።

የእኛ ህጐች መጽደቅ ስለሚያስፈልጋቸው ዓለምአቀፍ ውሎች ምንም ስለማይናገሩ ከፊርማ በኋላ ሊኖር የሚገባው ሥነ ሥርዓት ሁልጊዜ የውይይት አርዕስት ነው ። ይህንን ችግር በመፍታት ረገድ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1969 ዓ.ም. ቁጥር 5/4/ ብቁ እንዳልሆነ በበቂ መልክ ጠቁመናል [17] ። ይህን በተመለከተ በተቻለ ፍጥነት አንድ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል ። ሌላው ቢቀር የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀ መንበሩን ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1967 ዓ.ም. እንደወጣው ቁጥር 4 ያለ ድንጋጌ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1969 ዓ.ም. ውስጥ መግባት አለበት እንላለን ።

ባለፈው መንግሥት የተገቡ ውሎች በአሁኑ መንግሥት ላይ ያላቸውን ተፈ

[17] ይህ ከላይ በገጽ 6 እና 7 ላይ ተተንትኗል ።

ጸሚነት በሚመለከትም ፣ በመሠረታዊ የሁኔታዎች ለውጥ ምክንያት ዘመን ካለ ፈባቸው ዓለምአቀፍ ውሎች በስተቀር ሁሉም በአሁኑ መንግሥት ላይ አስገዳ ጆች ናቸው የሚል ግምት መወሰድ አለበት ።

የዓለምአቀፍ ውሎች ደረጃ ማለትም ከአገር ውስጥ ህጐች ጋራ የበላይ ወይም እቻ መሆናቸው ብዙውን ጊዜ የሚመለከተው የሕገ መንግሥት ሕገ ቃላ ትን ነው ። የአንዳንድ አገሮችን ሕገ መንግሥታት ስናወዳድር ዓለምአቀፍ ውሎች

ሀ. የአገሪቱ ህግ አካልና የአገር ውስጥ ሕጐች የበላይ እንደሆኑ ፤

ለ. የአገሪቱ ህግ አካልና ከአገር ውስጥ ህግ ጋር እቻ እንደሆኑ ፤

ሐ. የአገሪቱ ሕግ አካልና ከፌዴራል ህጐች ጋር እኩልና ፤ ከክልል መንግሥት ወይም ከክፍላተ ሀገራት ህጐች የበላይ እንደሆኑ ፤

መ. በግልጽ በሕግ ካልታወጁ በስተቀር የአገሪቱ ህግ አካል እንዳል ሆኑ ያሳየናል ።[18]

ዛሬ እኛ ሕገ መንግሥት የለንም ። በዚህና በሌሎችም ተጨባጭ ምክንያ ቶች የተነሳ በዚህ ጭብጥ ላይ አቋም አለመውሰዱ ይመረጣል ። የዚህን መልስ የሚሰጠን የአዲሲቱ ኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ወይም በዚሁ ላይ ተመስርቶ የሚወጣ የዓለምአቀፍ ውሎችን የሚመለከት ከፍተኛ ሕግ ይሆ ናል ።

---

[18] ኤች ፣ ክሊክስ ( ኢዲ ) ዘ ትሪቲ ሜክርስ ሀንድ ቡክ ኦሽኒያ ፐብሊኬሽን ፣ ኢንኮ ፣ አልምግ ሪያት ኤንድ ዊክሲል / ( 1973 ) ፣ ከገጽ 20 እስከ 30 ከአጠቃላይ ይመለከቷል ።